

# የኢየሱስ ተአምራት

## * ውኃን ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩ

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ ተአምሩን ያደረገው ቃላ ዘገሊላ በተባለ ስፍራ በነበረ አንድ የሠርግ ሥነሥርዓት ላይ ነበር።
የኢየሱስ ክርስቶስ እናት መጣችና ኢየሱስን ሠርገኞቹ የወይን ጠጅ አልቆባቸዋል አለችው። ኢየሱስም አገልጋዮቹን ጋኖቹን ውኃ እንዲሞሏቸው አዘዛቸው። እነርሱም ውኃ በጋኖቹ ውስጥ ሞሉ። ውኃ የተሞሉት ጋኖችም ወይን ጠጅ ተቀዳባቸው። ኢየሱስ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ቀይሮታልና። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 2፡ 1 - 11

## * ማዕበሉን ፀጥ ማድረጉ።

ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ልክ በጀልባ መጓዝ ሲጀምሩ ኃይለኛ ማዕበል ተነሳ። ኢየሱስ በጀልባዋ ላይ ተኝቶ ነበር። ደቀ መዛሙርቱ ግን በፍርሃት ተዋጡ። ኢየሱስን ቀሰቀሱት። ኢየሱስም ከእንቅልፉ ተነስቶ ማዐበሉን ገሰፀው ማዕበሉም ፈፅሞ ፀጥ አለ። ንፋሱም መንፈሱን አቆመ። ባህሩም ሰላማዊ ሆነ። ደቀ መዛሙርቱ አጅግ ገረማቸው! “ማዕበልና ወጀብ እንኳን ይታዘዙለታል።” አሉ። የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 8፡ 23 - 27

* <u>ፈውሶች።</u>

በኃይለኛ ንዳድ ታማ የነበረችውን የስምዖንን አማት ኢየሱስ ፈወሳት። ከዚያም ተነስታ አገለገለቻቸው።Matthew 8:14-15የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 8፡ 14 -15

በኢየሩሳሌም የሚኖርና ከልጅነቱ ጀምሮ እውር የነበረ ሰው ነበር። ኢየሱስም በዚህ ሰው አይኖች ላይ ጭቃ ካደረገበት በኋላ ሄዶ በሰሊሆም መጠመቂያ ሄዶ እንዲታጠብ አዘዘው። ሰውዬውም ጭቃውን ሲያጥበው አይኑ አየ። John 9: 1-41 የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 9፡ 1 - 41

ከእለታት አንድ ቀን አይነ ስውሩ ለማኝ በርጠሎሜወስ ኢየሱስን ስለፈውስ ምህረት ለመነው። ኢየሱስም ስለእምነቱ እንደተፈወሰ ነገረው። ከዚያች ሰዓት ጀምሮም ማየት ቻለ። እግዚአብሔርንም አከበረ። Mark 10: 46-52 የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 10፡ 46 – 52.

በቅርናሆም አንድ ሽባ ሰው ነበር። መራመድ ስለማይችል ወዳጆቹ ወደ ኢየሱስ ወሰዱት። ኢየሱስ በነበረበት ቤት ውስጥ እጅግ ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ስለነበር በበር በኩል ይዘውት መግባት አልቻሉም። ስለዚህ ጣራውን በስተው በጣራው ላይ ወደታች ኢየሱስ ወዳለበት ቦታ አወረዱት።

ኢየሱስም ሰውዬውን ኃጢአቱ እንደተሰረየለት ከነገረው በኋላ እንዲነሳ አዘዘው። ሰውዬውም አልጋውን ተሸክሞ ሄደ።

አንዳንድ ሰዎች በመጀመሪያ ኢየሱስን ተጠራጥረውት ነበር። ነገር ግን ይህ ሰው ተፈውሶ ቀጥ ብሎ በመካከላቸው ሲራመድ ሲያዩት ተደነቁ። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5፡ 17 -26

ለምፅ የነበረባቸው አስር ሰዎች ኢየሱስን እንዲፈውሳቸው ጠየቁት። ወደካህን ሄደው ራሳቸውን እንዲያሳዩ አዘዛቸው። እነርሱም በመንገድ ላይ እንዳሉ ተፈወሱ። ከእነርሱ አንዱ ብቻ ነበር ተመልሶ በኢየሱስ ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ኢየሱስን ያመሰገነው። Luke 17: 11-19 የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17፡ 11 – 19